# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

የግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 311 ሚያዝያ 17 2006


አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

ድሬዳዋ የኢትዮጵያዊያን ከተማ ነበረች። ኢትዮጵያዊያን የጎሳቸውን አጥር አፍርሰው በኢትዮጵያዊነታቸው ብቻ ለረዥም ዘመን አብረው በድሬዳዋ ኑረዋል። በዚህ ሁኔታ የሚኖረው ህዝብ አብሮ ስቆ ፤አብሮ ተደስቶ፤ ያለው ለሌለው አካፍሎና ተቻችሎ መኖርን የሚያውቅ ነበር። ዛሬ ግን ያች ቀድሞ የምናውቃት ድሬዳዋ ተረት ሁናለች። ሁሉ ስቆና ተደስቶ የሚኖርባት ከተማ ሳትሆን በየወቅቱ በእሳት እንድትጋይ ሁና ብዙዎች እንባቸውን በመዳፋቸው የሚያፍሱባት ከተማ ሁናለች። ብዙዎች የንግድ ሥፍራቸው ተቀነባብሮ በተነሳ እሳት በመጋየቱ ባዶ እጃቸውን ቀርተዋል።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## በአፋር ክልል በድምበር ግጭት የተፈጠረው ኑከት ተጠናክሮ መቀጠሉ ታወቀ

ባለፈው ቅዳሜ በአፋር ክልል የተነሳውን ህዝባዊ ተቃውሞ ተከትሎ በወያኔ ፌዴራል ፖሊስና የመከላከያ ሃይል ከ12 ሰላማዊ ዜጎች በላይ ከተገደሉ በኋላ በክልሉ ከፍተኛ ህዝባዊ የተቃውሞ እንቅስቃሴ እየተካሄደ መሆኑ ከአካባቢው ያገኘነው መረጃ ኧመለከተ::

ረቡእ እለት በሰመራ ከተማ የዱፍቲ 2ኛ ደረጃ ትምህርትቤት ተማሪዎች ሰላማዊሰልፈ በመውጣት መንገድ በመዘጋታቸው በወያኔው አጋዚ ፌዴራል ፖሊስና በክልሉ ልዩ ሃይል ታጣቂዎች ተኩስ በመከፈቱ በበረካታ ያካባቢው ዜጎች ላይ ከፍተኛ ጉዳት እንደደረሰ ለማወቅ ችለናል:: በዚሁ ጥቃት በበረካታ ወጣቶች ላይ ጉዳት የደረሰባቸው ሲሆን 3 ወጣቶች ደግሞ ከባድ ጉዳት እንደደረሰባቸው የደረሰን መረጃ ያመለክታል:: ከነዚሁ ከባድ ጉዳት ከደረሰባቸው ወጣቶች መካከል መሃመድ ሀሰን እና ወለዑ የተባለ የ 16 አመት ወጣት እንደሚገኙበት ሲታወቅ በክልሉ የሚገኘው ሆስፒታል በጥቃቱ ጉዳት የደረሰባቸውን ወጣቶች አናክምም ማለታቸውም ታውቋል::አንድ ስማቸው እንዳይጠቀስ የፈለጉ የሆስፒታሉ ሰራተኛ እንደገለጡት መመርያው የተላለፈላቸው ከባለስልጣናቱ እንደሆነና ለተጎዱት ወጣቶቸ የህክምና እርዳታ ቢያደርጉ በአገዛዙ ባለስልጣናት ችግር ሊፈጠርባቸው እንደሚችል ገልጠዋል:: ይህ በእንዲህ እንዳለ የወያኔው ጉጅሌ አገዛዝ ባካባቢው የተፈጠረው ተቃውሞ እጅግ ስላሳሰበው ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ታጣቂዎችን ወደ አፋር ክልል ያንቀሳቀሰ ሲሆን የሰመራ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ከሌሎች የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ጋር እንዳይቀላቀሉ ገቢው በታጣቂዎችና በፌዴራል ፖሊሶች እንደተከበበ ለመረዳት ችለናል:: ( ወደ ገጽ 2 ዞሯል )

## ሕወሃት ዜጎችን ያለ ርህራሄ መጨፍጨፉን እንደቀጠለ ነዉ

ሰሞኑን በአፋርና ሶማሌ ክልሎች በድንበር ማካለል ሰበብ በተነሳ ውዝግብ ሕወሃት ልክ ከዚህ በፊት እንደሚያደርገው ችግሩን በማረጋጋት ሰበብ ገብቶ ንጹሃን ዜጎችን መጨፍጨፉ ተጠቆመ። ባለፈው ሳምንት መጨረሻ አካባቢ በሁለቱ ክልሎች ሕዝቦች መካከል የተነሳው ውዝግብ ከቁጥጥር ውጭ ከመሆኑ በፊት መቆጣጠር አለብኝ ብሎ ያመነው ሕወሃት፤ ፌደራል ፖሊሶችን በመላክ በማረጋጋት ፋንታ ከ12 ሁለት በላይ አፋሮችን ገድሎ ብዙዎችን ማቁሰሉ ያበሳጫቸው የአፋር ክልል ሕዝቦች በከፍተኛ ቁጥር በመውጣት ወደ ጅቡቲ የሚያደርሰውን ዋና መንገድ አዋሽ 7 ኪሎ ላይ በመዝጋት ተቃውሟቸውን ሲገልጹ መዋላቸው ታውቋል። የመንገድ መዝጋቱ ተቃውሞ እስከ ቅዳሜ እኩለ ቀን ድረስ የቀጠለ ሲሆን ችግሩን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታትና የተሻለ መፍትሄ ለመፈለግ በሚል ያፋር ክልል የወያኔ ቁንጮዎች ኢስማኤል አሊሴሪና አወል አርባ እንዲሁም አጋር የሚባለው የአፋር ክልል ፓርቲ መሪ ጣሃ አህመድ በቦታው የተገኙ ቢሆንም ከሕዝቡ በደረሰባቸው ከፍተኛ ተቃውሞ ምክንያት አካባቢውን በፍጥነት ጥለው መሄዳቸው ታውቋል። ለተቃውሞ የወጣው ሕዝብ “አስጠቃችሁን፣ እናንተ የሕወሃት እንጅ የኛ ተወካዮች አይደላችሁም፣ የምትናገሩትም ሆነ የምታደርጉት ለሕወሃትና ለራሳችሁ ጥቅም ብቻ ነው። ስለሆነም አንፈልጋችሁም። ከዚህ አካባቢ ጥፉልን” በማለት በከፍተኛ ጩኸት እንዳባረራቸው ታውቋል።

ክልሉን እየመራን ነው የሚሉት ገዥዎች ካካባቢው ተባረው ከወጡ በኋላ የተቃዋሚው ሕዝብ ቁጥር ከመጠን በላይ እየጨመረ በመምጣቱና ተጠቃን የሚለው የአፋር ሕዝብ ምሬት እያየለ በመምጣቱ ሕወሃት ለሌላ ግዳይ ከፍተኛ ቁጥር ያለው የአጋዚ ጦር ወደ ስፍራው መላኩም ታውቋል። በስፍራው የነበሩና ሁኔታውን የተከታተሉ ታዛቢ እንደሚሉት የሕዝቡን ቁጣ እጅግ ያባሰው ከሟቾቹ የሚበዙት ከሕወሃት ፌደራሎች በቀጥታ ( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

## የኢትዮጵያ አየር መንገድ ባልታወቀ ችግር ምክንያት ተገዶ ሮም ማረፉ ተሰማ

በበረራ ቁጥር ኢቲ 500 የተመዘገበና ከአዲስ አበባ በሮም ወደ አሜሪካ ይጓዝ የነበረ ድሪም ላይነር ዘመናዊ አውሮፕላን በድንገት ባልታወቀ ምክንያት ተገዶ ሮም ማረፉ ታውቋል። ሕወሃት ልምድ ያላቸውንና እውቅ አብራሪዎችንና የበረራ ቴክኒካኒስቶችን በጥርጣሬና በአመለካከታቸው ስላልፈለጋቸው ብቻ እያባረረ በውጭ ሰዎች መተካት ከጀመረ ወዲህ በተደጋጋሚ ከፍተኛ ችግር እያጋተመው መሆኑም ተያይዞ ተጠቅሷል። በሀገሪቱ ዘርንና አመለካከትን መሰረት ያደረገው የወያኔ የሰራተኛ ምደባ ዝነኛ ወደ ነበረው የሀገሪቱ አይር መንገድ ከገባ ዓመታትን እንዳስቆጠረ የሚናገሩ ታዛቢዎች ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የወያኔው አየር መንገድ በችሎታ ማነስ የተነሳ የመለማመጃ አውሮፕላኖችንና የጥገና መሳሪያዎችን ከማቃጠልና ከመሰባበር ጀምሮ የተሳፋሪን ሂዎት አደጋ ላይ እስከመጣል ደርሷል ይላሉ።

በቅርቡ ተጠልፎ ሲዊዘርላንድ ዉስጥ ያለረፈዉን አዉሮፕላን ጨምሮ ወያኔ ስልጣን በያዘባቸዉ አመታት ዉስጥ ዝነኛዉና በአፍሪካ ወደር የለዉም ተብሎ የሚነገርለት የኢትዮጵያ አየር መንገድ ተደጋጋሚ እክሎች አጋጥመዉታል። አየር መንገዱ ከገጠመዉ ሰዉ ሰራሽና መካኒካል ችግሮች ዉጭ የወያኔ ዘረኛነት አሰራር ያንገፈገፋቸዉ ብዙ በአቭየሺን አስተዳደርና በበረራ የረጂም ግዜ ልምድ ያካባቱ ሰዎች አየር መንገዱን በመልቀቃቸዉ አየር መንደጉ ችግር ላይ መዉደቁ በመሰማት ላይ ነዉ። ይህ ችግር ያሳሰባቸውና የተማረሩ ሰራተኞች ድርጅቱን እየጣሉ በመሰደድ ወደ ሌሎች አየር መነገዶች በመቀጠር ላይ እንደሆኑ የሚጠቁሙት ታዛቢ አንዳንዶቹ ደግሞ ልክ ባለፈው እንዳየነው የሚያበሩትን አውሮፕላን በመጥለፍ ተቃውሟቸውን እየገለጹ እንደሆነ ገልጸዋል። ከጥቂት ሳምንታት በፊት በኢትዮጵያዊው ምክትል አብራሪ የተጠለፈው የኢትዮጵያ አውሮፕላን ስዊዘርላንድ ማረፉ አይዘነጋም።

## የፌዴራል ዋና ኦዲተር ውጭጉዳይና መከላከያ ውስጥ አሁንም ከፍተኛ የገንዘብ ጉድለት መኖሩን አመለከተ

በሙሰኝነት ላይ የተገነባዉ የወያኔ ስርዐት በአንድ በኩል ሙሰኝነትን አኢዋጋለሁ እያለ ከአገዛዙ ቁንጮዎች ጋር የፖለቲካ ቅራኔ ዉስኢጥ የገቡትነ አንዳንድ ሰዎችነ ሲያስር በሌላ በኩል ደገሞ በተቋም ደረጃ አገሪቱ ዉስጥ የሚፈጸመዉ ይህ ነዉ ተብሎ የማይነገር መጠነ ሰፊ ሙስና አሁንም በተለይ መከላከያን በመሳሰሉ ትልልቅ ተቋሞች ዉስጥ እነደቀጠለ መሆኑን የግነቦት ሰባት ድምጽ ዘጋቢዎች ከአዲስ አበባ በላኩልነ ዜና ገለጹ። የመከላከያ ተቋም ከዚህ ቀደምም የፌዴራሉ ዋና ኦዲተር ገንዘብ ይባክናል ብሎ ለፓርላማዉ ካቀረባቸዉ መ/ቤቶች ዉስጥ አንዱ ሲሆን ፓርላማዉ ጭራሽ መከላከያ በኦዲተሮች እንዳይታይ ህግ ማዉጣቱ የሚታወስ ነዉ።

የፌዴራል ኦዲተር መ/ቤት ዋና ኦዲተር የሆኑት አቶ ገመቹ ዱቢሶ የ2005 ዓ.ምየኦዲትሪፖርታቸውን ለፓርላማ ባቀረቡበት ወቅት በ132 የመንግሥት መ/ቤቶች ላይ በተካሄደው ኦዲት ከፋይናንስ ሥርዓት፣ ደንብናመመሪያ ጋር የሚጋጩ በርካ ታግድፈቶች መታየታቸውን አመልክተዋል፡፡ የትምህርት ተቋማትና መከላከያ ከፍተኛ የገንዘብ ጉድለት ከተገኘባቸው መስሪያ ቤቶች መካከል በቀዳሚነት ተጠቅሰዋል። ዋና ኦዲተሩ ባቀረቡትና 54 ያህል ገጾችን በያዘው በዚሁ ሪፖርታቸው ሂሳብ በወቅቱ ያለማወራረድ ችግር፣ የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ ተመዝግቦ መገኘት፣ ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ ግዥዎችን መፈጸም፣ የጥሬ ገንዘብ ጉድለቶች፣ ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## በአፋር የተነሳውን ተቃውሞ ተከትሎ 8 ሰዎች በፌደራል ፖሊሶች ተገደሉ

ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ ሆን ብሎ በፈጠረዉ ችግር የተነሳ ኢትዮጵያ ዉስጥ በድንበርተኛ ብሄረሰቦች መካከል የሚፈጠረዉ ግጭት እየተበራከተ መምጣቱንና አገሪቱን ወዳልተፈለገ አቅጣጫ እየገፋት መሆኑን ከወደ አዲስ አበባ የሚደርሱን ዜናዎች ያስረዳሉ። ይህንን አሰመልክቶ ደቡብ ኢትዮጵያ ለረጂም ግዜ በጎሳ ግጭቶች እየተናጠ የቆየ ሲሆን ከሰሞኑ ደግሞ ቁርቁራ እየተባለ በሚጠራው አካባቢ በአፋር እና በሶማሊ ጎሳ አባላት መካከል የተነሳውን ውዝግብ ተከትሎ የፌደራል ፖሊስ በወሰደው እርምጃ 8 ሰዎች መገደላቸውን የአካባቢው ሰዎች እና የአፋር ሰብአዊ መብቶች ድርጅት ሲገልጽ፣ አፋር ህዝብ ፓርቲ ባወጣው መግለጫ ደግሞ የሟቾቹን ቁጥር 12 አድርሶታል።

( ወደ ገጽ 4 ዞሯል )

## የዘረኞች ነውር በድሬዳዋ !!

ድሬዳዋ የኢትዮጵያዊያን ከተማ ነበረች። ኢትዮጵያዊያን የጎሳቸውን አጥር አፍርሰው በኢትዮጵያዊነታቸው ብቻ ለረዥም ዘመን አብረው በድሬዳዋ ኑረዋል። በዚህ ሁኔታ የሚኖረው ህዝብ አብሮ ስቆ ፤አብሮ ተደስቶ፤ ያለው ለሌለው አካፍሎና ተቻችሎ መኖርን የሚያውቅ ነበር። ዛሬ ግን ያች ቀድሞ የምናውቃት ድሬዳዋ ተረት ሁናለች። ሁሉ ስቆና ተደስቶ የሚኖርባት ከተማ ሳትሆን በየወቅቱ በእሳት እንድትጋይ ሁና ብዙዎች እንባቸውን በመዳፋቸው የሚያፍሱባት ከተማ ሁናለች። ብዙዎች የንግድ ሥፍራቸው ተቀነባብሮ በተነሳ እሳት በመጋየቱ ባዶ እጃቸውን ቀርተዋል። ልጆቻቸውም ድሃ አደግ እንዲሆኑ ሁኗል። ይባስ ብሎ ንብረቶቻቸውን ከእሳት ቃጠሎ ለመከላከል እሳቱን ለማጥፋት የተነሱ ዜጎች በአሸባሪነት ተከሰው ህወሃቶች "ፍርድ ቤት" ብለው ወደ ሚጠሩት ሥፍራ እንዲቀርቡ ሁኗል።

ገ/መድህን ገ/መስቀል፤ ቢኒያም ጌታቸው፤ መቻል አብራር፤ ምትኩ ውብየ፤ ኢዮብ ገብሬ፤ ሃቢብ ሽምሱ፤ ለዒላ ዓሊ ፍትህን በማያውቀው በህወሃት ፍርድ ቤት ቀርበዋል። ከእነዚህ ውስጥ ከገ/መድህን ገ/መስቀል በቀር ሌሎቹ የዋስ መብት ተነፍጓቸው ወሂኒ እንዲቆዩ ተደርጓል። ገ/መድህን ገ/መስቀል በምን ሁኔታ ከሌሎቹ ተለይቶ "ነፃ ሰው" ሊባል እንደቻለ የሚያውቅ የለም። ብዙ ሰዎች ግን በትግራይ ተወላጅነቱ አፍቃሬ ህወሃት " ተደርጎ እንዲታይ ለማድረግ ነው ይላሉ። ህወሃት በልዩ አፈና የራሱ ዋሻ ያደረገውን የትግራይ ህዝብ ከሌላው ኢትዮጵያዊ ወገኑ ለማቆራረጥ እንዲህ አይነት ያፈጠጠና ያገጠጠ የዘር መድልዎ ሲያደርግ የመጀመሪያው አይደለም። ድህረ ምርጫ 97 ከአዲስ አበባ ከተማ ተግዘው ወደተለያየ ማጎሪያ ከተላኩት በርካታ ሺዎች ውስጥ የትግራይ ተወላጆችን መርጦ "እናንተ ነፃ ናችሁና ወደ ቤታችሁ ሂዱ" ብሎ እንዳሰናበተ የማያውቅ የለም። የዘረኞቹ ቁንጮ መለስ ዜናዊ በህይወት በነበረበት ወቅት ሲደረግ የነበረውና ከህልፈቱም ቦኋላ ቀጥሎ ያለው የህወሃት የዘረኝነት መገለጫ አንዱ መንገድ ይሄው ነው። በትግራይ ወጣቶች የህወት መስዋዕትነት ለስልጣን በቅተው እራሳቸውን ያነገሱ የህወሃት መሪዎች ትግሬን ነፃ ማውጣት ማለት ከሌላው ወገኑ ጋር ውሎ አድሮ ደም የሚያቃባ አድልአዊነት እንዲህ በአደባባይ መፈጸም ነው ብለው ያምናሉ። እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል እንዳለቺው እንስሳ ለህወሃቶች እንዲህ አይነት ዘረኝነት ወደፊት ሊፈጥር የሚችለው አደጋ አይታያቸውም ወይም ስለርሱ ማሰብ አይፈልጉም። ።ከአማራና ከአፋር የሚዋሰኑትን ለም ቦታዎችንና በበከርሰ ምድር ማዕድን የከበሩ ሥፍራዎችን ቀምተው ወደ ክልላቸው ሲጠቀልሉና ነዋሪውን በማፈናቀል የቀድሞ ታጋዮቻቸውን ሲያሰፍሩባቸው አልሰቀጠጣቸውም። ወያኔ የራሱ ዋሻ አድርጎ በሚቆጥረው የትግራይ ክልል ውስጥ እያደረሰ ያለው ስቃይና መከራ የክልሉን ግንብ ጥሶ በመላው አለም በመሰማት ላይ ባለበት በአሁኑ ወቅት በተለያየ የአገሪቱ ክፍል ተበትኖ የሚኖረውን ጥቂት የትግራይ ተወላጅ ተጠቃሚ በማድረግ የትግሬ ነጻ አውጪ ለመምሰል የሚደረገው ጥረት በትግራይ ህዝብ ዘንድ ሳይቀር እየተወገዘ ነው። ዘረኞቹን የህወሃት መሪዎች እረፍት የነሳውና እንዲቅበዘበዙ እያደረገ ያለውም የዚህ ዘረኛ አላማቸው የራሴ ነው በሚሉት የቀድሞ ምሽጋቸው ሳይቀር እየታወቀ መምጣቱ ነው።

ዛሬ ከትግራይ ጀምሮ በመላው አገሪቱ ማለት ይቻላል የወያኔን ዘረኝነትና ዘረፋ የሚቃወሙ ሁሉ ሥልጣንን በተቆጣጠሩ በእነዚህ ዘረኞች እጅ የመከራ ፅዋቸውን እየተጎነጩ ነው። የአሬና አመራርና አባላት ብቻ ሳይሆን በቤተሰቦቻቸው ጭምር ላይ ትግራይ ውስጥ እየተፈጸመ ያለው ግፍ የሚያረጋግጠው ይህንኑ ሃቅ ነው። የታገልነውና የደም መስዋዕትነት የከፈልነው እናንት ጥቂት ዘረኞችንና ቤተሰቦቻችሁን በራሳችን ላይ ለማንገስ አልነበረም እያሉ ያሉ እንደነ አቶ አሰግድ ገብረስላሴ ያሉት ልጆቻቸው ጭምር በጎዳና እየተደበደቡ እስር ቤት ሲወርወሩ ነፍሳቸውንና ስጋቸውን ለህወሃት መሪዎች ያስረከቡት ጥቂት የትግራይ ተወላጆች ግን ከዘረፋ በተገኘ ሃብት ቢጠሩዋቸው የማይሰሙ ዲታ ሆነዋል። በልማትና እድገት ሥም በጋምቤላ ድሆችን ከኖሩበት መሬት አፈናቀለው እና ሜዳ ላይ በትነው መሬት ከተቀራመቱት ባዕዳን በቁጥር የሚበልጡት የዘረኞቹ ጋሻ ጃግሬ የሆኑ ትግሬዎች ናቸው። በአዲስ አበባ በዜጎች ደምና አጥንት ላይ የተገነቡ የትላልቆቹ ህንፃ ባለቤቶች የፋሽስቱ የህወሃት አባላት ናቸው። የአገሪቷን የንግድ ማዕከል ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ ተቆጣጥረው በዚያች አገር የሚዘባነኑት እነዚሁ በትግራይ ሥም የሚነግዱ ቡድኖች መሆናቸውን ህዝቡ የሚያውቀው እውነት ነው።ለትግራይ ነፃ አውጪዎች ሲባል የመከራውን ፅዋ በመጎንጨት ላይ ያለው ህዝብ ቁጣ የዶፍ ዝናብ ሊጥል የተዘጋጀ ሰማይን ይመስላል።ያ ቁጣ የፈነዳ ግዜ የሚያቆመው ምዳራዊ ኃይል እንደሌለ በሚቾት የደነዘዘው የህወሃት አመራር የተገነዘበው አይመስልም።

ስለዚህ ዘረኛና ወንጀለኛ ቡድን እጅግ የሚያሳዝነው ሌላው ነገር 23 አመት ሙሉ የአገሪቱን በትረ ሥልጣን እንዳሻው እያሽከረከረም ቢሆን ከመንደርተኝነት ስሜት ሊላቀቅ አለመቻሉ ነው። ዛሬም እንደትናንቱ ትግራይን መደበቂያ ዋሻ ፤ ዞሮ ዞሮ መግቢያ ለማድረግ የማይፈነቅለው ድንጋይ የለም። ቅድሜ ወያኔ የአገሪቱ ህዝብና መንግሥት ንብረት የነበሩ ንግድ ድርጅቶችን በመውረስ የደለበና ዛሬ በአገሪቱ ብቸኛ የሥራ ተቋራጭ፤ ዕቃ አቅራቢና አገልግሎት ሰጪ የሆነው ኢፌርት በስም የትግራይ ህዝብ በተግባር ግን የህወሃት ባለሥልጣኖች የገቢ ምንጭ መሆኑን ያልተረዳ የለም።መመኪያ ዋሻየ ከሚለው የትግራይ ህዝብ መነጠሉን እየተረዳ የመጣው ይሄ ፋሽስታዊ አስተሳሰብ ያለው ነውረኛ ቡድን ሰሞኑን ሌላ አሳፋሪ ድርጊት እየፈፀመ ነው። "ከትግራይ ህዝብ ጋር መታረቅ" የሚል ዜማ ይዞ ብቅ ብሏል። ህወሃት የነፃ አውጪ ስሙን እንኳን ሳይቀይር የ80 ሚሊዮን ህዝብ ገዢ እኔ ነኝ ብሎ ድርቅ ማለቱን እናውቃለን። ስማችሁን ቀይሩና አገሪቷን ግዙ ቢባሉም በጀ አላሉም። ይሄን ስም ይዘው በትግራይ ህዝብ ላይ ተንጠላጥለው አገሪቷን ሲዘርፉ ኖሩ። በዚህም ዘረፋ ትናንት ወደ ሥልጣን ሲመጡ ሲሙኒ እክሳቸው ውስጥ ያልነበራቸው ዛሬ በዓለማችን ከሚታወቁ ሃብታሞች ተርታ ለመግባት ችለዋል። መሪያቸው የነበረው መለስ ዜናዊ 3 ቢሊየን ዶላር ባለቤት በመሆን ከዓለም ሃብታም መሪዎች ተርታ ስሙ የሚነሳ ሁኗል። ሌሎችም እንደየአቅማቸው በሚሊየን የሚቆጠር ንብረት ዘርፈው ኢንቨስተሮች እኛ ነን ብለዋል። በትግራይ ነጣ አውጪነት ሥም ተደራጅተው የብዙ ንፁሃን ዜጎችን ደም አፍሰው፤ ብዙዎችን ለስደት ዳርገው፤ የብዙ ዜጎችን ቤተሰብ በትነው ሲያበቁ የትግራይን ህዝብ ይቅርታ እንጠይቅ ተባብለው ትግራይ ወርደዋል። ይሄን የሰማ ሌላው ህዝብ ሊሰማው የሚችለውን ቁጣ የትግራይ ህዝብ ያጣዋል ብለን አናስብም።ሌላው በተበደለ፤ ሌላው በተገፋ፤ ሌላው ጦሙን ባደረ፤ ሌላው ለስደት በተዳረገ የትግራይ ህዝብ ይቅርታ የሚጠየቅበት ምክንያት ምን እንደሆነ ግልፅ አይደለም። ለማንኛውም የትግራይ ህዝብ የህወሃት ዋሻና መደበቂያ አልሆንም ብሎ እንቅስቃሴ ጀምሮአል። ይሄ እጅግ የሚደገፍና ግዜው የሚጠይቀው የሞራል ግዴታም ነው። በትግራይ ሥም ተደራጅተው "ለትግሬ ብለን" እያሉ የንፁሃንን ደም ሲያፈሱ እና ቤተሰብ እየበተኑ ሜዳ ላይ ሲጥሉ እያዩ ዝም ማለት የግፉ ተባባሪ ያደርጋል እንጂ ከደሙ የሚያነፃ አይሆንም። ለዚህም ነው የትግራይ ህዝብ ወያኔ በስሙ መነገዱን እንዲያቆም ጠመንጃ ይዞ እስከመፋለም የተነሳው። የትግራይ ህዝብ ዲሞክራሲያዊ ድርጅት /ደሚት/ የትግል አላማ ይህንን ወያኔ የፈጠረውን ጥላቻ የመስበር ተልዕኮ ያለው ነው። የትግራይ መሬትና የትግራይ ህዝብ ከእንግዲህ የወንጀለኛው ህወሃት መደበቂያ ዋሻ አይሆንም።

ህወሃት ከህዝብና ከአገር ለመታረቅ ከፈለገ በትግራይ ሥም ላለፉት 23 አመታት ለፈጸመው ወንጀል ይቅርታ ፍለጋ ትግራይ መንደሮች ድረስ መዝለቅ አይጠበቅበትም። ከትግራይ ውጪ ተጀምሮ ትግራይን ባጥለቀለቀው ኢፍትሃዊነት፤ ግፍና መከራ ጸጸት ከተሰማው ሥልጣን ለመልቀቅ መዘጋጀትና ለኢትዮጵያዊያን ለማስረከብ በመወሰን እዚያው ምንሊክ ቤተመንግሥት ሆኖ አዋጅ ማስነገር ይችላል። ለዚህ ዝግጁነት ተግባራዊ እርምጃ ለምሳሌ የታሰሩትን የፖለቲካ እስረኞች፤ ጋዜጠኞች፤ የሃይማኖት መሪዎችን መልቀቅ፤ የሥልጣን ማስጠበቂያ አድርጎ በዘረኝነት መስፈርት የገነባውን የአፈና ተቋማት ማፍረስ፤ ህዝብ ሃሳቡን በነጻነት የሚገልጽበትንና መሪዎቹን በነጻነት የሚመርጥበትን ዕድል በመፍቀድ ማረጋገጥ ይችላል።

ይህ እስካልሆነ ድረስ ከአደዋ ወይም ከሽሬ የወያኔን ዕድሜ የሚያራዝም ይቅርታ ጨርሶ የሚታሰብ አይደለም። በ23 አመት የሥልጣን ዘመን የተገኘው ዘረፋ አልበቃ ብሎ ሥልጣን ላይ ለመንጠልጠል መንከላወስ ውጤቱ ሁሉንም ማጣት ነው።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

---

## በአፋር ክልል በድምበር ግጭት የተፈጠረው ጉከት

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

ይሁን እንጂ በአገዛዙ ታጣቂዎች በተወሰደባቸው ኢሰብአዊ ጭፍጨፋ እጅግ የተበሳጩ የአፋር ክልል ነዋሪዎች ህሙስ እለት ታላቅ የተቃውሞ እንቅስቃሴ ለማድረግ እየተዘጋጁ እንደሆነ የደረሰን መረጃ ያመለክታል። የአፋር ህዝብ በተከታታይ በወያኔ ጉጅሌ አገዛዝ ከፍተኛ ግፍና በደል ከሚፈፀምባቸው ኢትዮጺያውያን መካከል አንዱ ሲሆን ፋሺስቱ የወያኔው ቁንጮ ለገሰ ዜናዊ የኢትዮጵያን ሰንደቅአላማ ባራከሰበት እና ባዋረደበት ወቅት በድፍረት የኢትዮጵያን ሰንደቅአላማ ያውለበለቡና በኢትዮጵያዊነታቸው እጅግ የሚኮሩ መሆናቸውን ባደባባይ ያስመሰከሩ ሲሆኑ መሪያቸውም የተከበሩ ሱልጣን አሊሚራህ ስለ ኢትዮጵያ ሰንደቅአላማ ሲናገሩ የኢትዮጵያን ሰንደቅአላማ እንኳን እኛና ግመሎቻችንም ያውቋታል በማለት ለህገራቸውና ለሰንደቅአላማቸው ያላቸውን ፍቅር እና ክብር መግለፃቸው ይታወሳል።

---

# ይቅርታ ትዉልድን ማቀራረቢያ እንጂ የዘረኞች ማሾፊያ ፌዝ አይደለም

“ጉድ ሳይሰማ መስከረም አይጠባም” ይላል የአገራችን ሰዉ። እዉነቱን ነዉ፤ ታሪካችንን ወደኋላ ዞር ብሎ ለተመለከተዉ ጉድ ሳይሰማ መስከረም አይጠባም። የዘንድሮዉ ነገራችን ግን ከጉድም ጉድ የጉድ ጉድ ነዉ። ኃብታችን አየተዘረፈ፤ ድንበራችን አየተሸረፈ’፤; ታሪካችን እየተበረዘ፤ ባህላችንም እየተከለሰ ነዉ። ነገር በምሳሌ ጠጅ በብርሌ እያልን የምናንቆረዉራቸዉ ተረቶቻችን ለዛቸዉ እየጠፋ ነዉ፤ መጪዉ ትዉልድ ሆን ተብሎ ካገሩ ቋንቋ ይልቅ የባዕዳን ቋንቋ ናፋቂ እንዲሆን እየተደረገ ነዉ። እንደዚህ አይነቱን ተነግሮ የማያልቅ ጉድ ይዞብን የመጣዉ ወያኔ ነዉ፤ ሆኖም ወያኔ ከነጉዱ ረግጦ እየገዛን አንዲኖር የፈቀድንለት እኛዉ እራሳችን ስለሆንን ማናችንም ምን ጉድ መጣብን ብለን መጠየቅ አንችልም።

ታሪካችን እየተምታታ፤ ባህላችን እየተከለሰ ተረቶቻችንም ለዛቸዉን እያጡ ነዉ የምንለዉ ንግግር ለማሳመር ብለን እንዳይመስላችሁ፤ እንደ ሰማይና ምድር ያረጀዉ ታሪካችን እኛኑ በሚመሩ ሰዎች የመቶ አመት ታሪክ ነዉ ተብሏል። አንዳንድ ተረቶቻችን ደግሞ ዘረኞቹ የወያኔ መሪዎች ተሸክመዉ ባመጡት ጉድ ለዛቸዉን አጥተዋል፤ ለወትሮዉ “ጉድ ሳይሰማ መስከረም አይጠባም” ነበር የሚባለዉ። ዘንድሮማ ..... የምን መስከረም ! በየቀኑ ሁለትና ሦስት ጉድ ሳይሰማ ሰኞ በማክሰኞ አይተካም። እያንዳንዱ ቀን ጆሯችን ዉስጥ ገብተዉ አዕምሯችንን ለካንሰር የሚዳርጉ ብዙ ጉዶች አሉት።
ወያኔዎች በ1998 ዓም አዲስ አበባን ሲቆጣጠር የሸበተዉን ታሪካችንን መቶ አመት ብለዉ ቆጠሩት፤ በጀግኖች ደም አምራና ደምቃ የምትዉለበለበዉን ባንድራችንን ጨርቅ ብሎ አሾፉባት። እኛም ከዚህ የበለጠ ምን ጉድ ይመጣል ብለን አንገታችንን ደፍተን ዝም አልን። አምቦ ላይ ገደሉን፤ አርባ ጉጉ ላይ ገደል ዉስጥ ገፍተዉ ጨመሩን፤ በደኖ ላይ በቢለዋ እንደ ጥሬ ስጋ ከተፉን፤ እግዚኦ ከዚህ የባሰ አታሳየን ብለን ዝም አልን። አሰፋ ማሩን በጠራራ ፀሐይ ህይወቱን ቀሙት፤ አለቃ ገ/ሥላሤን ማምለኪያ ቦታዉ ላይ አፍነዉ ገደሉት፤ አቤት የፈጣሪ ያለህ ብለን አሁንም ዝም አልን። በ1997ዓም ከ200 በላይ ወጣት፤ ሴት፤ ወንድ አረጋዊና ህፃን ሳይለዩ በመትረየስ ጨፈጨፉ፤ ሲበዛብን ግዜ አንድ ሰሞን ኡኡ ብለን አፋችንን ዘጋን። ዝምታ ዝምታን ፍርሃት ፍርሃትን እየወለደ የግድያዉ፤ የሰቆቃዉና የስደቱ ብዛት መሸከም እስኪያቅትን ድረስ እየባሰበት ሄዶ ይኼዉና ዘንድሮ ላይ ደረስን።

የወያኔ ዋነኛዉ ተልዕኮ እኛን አደህይቶ እሱ ሊከብር፤ በኛ ስቃይና መከራ እሱ ስልጣኑን ማራዘም ነዉ። ለዚህ ነዉ ወያኔና የቅርብ አጋሮቹ እየፈኩና እየደመቁ ሲሄዱ የኢትዮጵያ ህዝብ ግን መኖሪያ ቤቱን እላዩ ላይ ሲያፈርሱበት ሞራሉ እየላሸቀ፤ ልጆቹን ከጉያዉ ዉስጥ አዉጥተዉ ሲገድሉበት ልቡ እየደቀቀ የተፈጠረበትን ቀን የሚራገመዉ። ትናንት አይናቸን እያየ የተጠቃቀመ ቁምጣ ሱሪና ኮንጎ ጫማ አድርገዉ አዲስ አበባ የገቡት ወያኔዎች ዛሬ የሰማይ ጠቀስ ህንፃዎች፤ የትላልቅ እርሻዎችና የንግድ ድርጅቶች ፤ የባንኮችና የኢንሹራንስ ድርጅቶች ባለቤቶች ሆነዋል። የኢትዮጵያ ህዝብ ግን የንግድ ድርጅቱ በእሳት እየጋየበት፤ መኖሪያ ቤቱ እላዩ ላይ እየፈረሰበት፤ ገበሬዉ ከመሬቱ ነጋዴዉ ከንግዱ እየተፈናቀለ እናት አገሩን ለወያኔ አንድ ህይወቱን ደግሞ ለፈጣሪ እየተወ አንገቱን አቀረቀረ። ሰዉ ምን ይለናል የሚል ኢትዮጵያዊ ይሉኝታ ቀርቶ ፈሪሃ እግዚአብሄር የሚባል የሂሊና ሚዛናዊነት አብሯቸዉ ያልተፈጠረዉ የወያኔ ዘረኞች ዝም ባልናቸዉ ቁጥር ይበልጥ እየገደሉንና አንገታችንን ባቀረቀርን ቁጥር ቁልቁል እየኮረኮሙን የህግ አክባሪዎች አገር የነበረችዉን ኢትዮጵያችንን የህገ አራዊት አገር አደረጓት።

የኢትዮጵያ ህዝብ አስተዋይና የበደሉትን ይቅር የሚል ትልቅ ልብ ያለዉ ህዝብ ነዉ። የእንግዴ ልጅነታቸዉ ወደኋላ እየጎተታቸዉ ነዉ እንጂ የወያኔ መሪዎችም ቢሆኑ ይቅርታና ይቅር ባይነትን ከሚሰብኩ ሁለት ዋና ዋና የኢትዮጵያ ሐይማኖቶች አንደኛዉ የበቀለበት አፈር ላይ አብረዉ የበቀሉ ሰዎች ናቸዉ። ዘረኞቹ የወያኔ መሪዎች ይህንን በጅምላ የሚገድሉትን፤ መብቱን በጠየቀ ቁጥር እስር ቤት የሚወረዉሩትንና በዘረኝነት አለንጋ የሚለበልቡትን ህዝብ ይህንን ሁሉ በደል ፈጽመዉበትም ቢሆን ጥፋት አጥፍተናልና ማረን ብለዉ ይቅርታ ቢጠይቁ የኢትዮጵያ ህዝብ ሙስሊሙም ክርስቲያኑም ይቅር ባይ ነዉና ይቅር ይላቸዋል። እንደፍየል ወጠጤ ልባቸዉ ያበጠዉ ዕብሪተኞቹ የወያኔ መሪዎች ግን የረገጡት፤ያሰሩት፤ የደበደቡትና የገደሉት ሁሉንም የኢትዮጵያ ህዝብ ሆኖ ሳለ ዳግመኛ አይለምደንም ይቅር በለን ብለዉ ከአዲስ አበባ ትግራይ ድረስ ሄደዉ ይቅርታ የጠየቁት የትግራይን ህዝብ ነዉ። እነዚህ ገንዘብንና የተወለዱበትን ዘር እንደ ጣዖት የሚያመልኩ የሂሊና ደሃዎች ለኢትዮጵያ ህዝብና ለታሪኩ ከፍተኛ ንቀትና ጥላቻ እንዳላቸዉ በተደጋጋሚ ያሳዩን ቢሆንም ጥላቻቸዉንና ንቀታቸዉነ እንደዚህ በረከሰና ርካሽ በሆነ መንገድ ይገልጻሉ ብሎ ማንም አልገመተም። ኢትዮጵያን እመራለሁ የሚል አካል የሚምለዉ በትግረይ ስም፤ የሚኖረዉ ለትግራይ ህዝብ፤ ድፍን አገርን በድሎ ይቅርታ የሚጠይቀዉም ይህንኑ የትግራይን ህዝብ ከሆነ የዚህ ትልቅ ብሔራዊ ችግር ባለቤት ወያኔ ወይም በስሙ የሚነገደዉ የትግራይ ህዝብ ሳይሆን ባጠቃላይ የኢትዮጵያ ህዝብ ነዉ፤ ችግሩን የማስወገድ ሀላፊነት ያለበትም የኢትዮጵያ ህዝብ ነዉ።

እዚህ ላይ የትግራይን ህዝብ ጨምሮ ሌላዉ የኢትዮጵያ ህዝብም ሆነ ይህንን የዕብሪተኞች ቅሌት የተመለከተ ማንም ሰዉ ልብ እንዲለዉ የምንፈልገዉ አንድ ሃቅ አለ፤ እሱም ኢትዮጵያን እንመራለን የሚሉ ሰዎች በህዝብ ላይ ለፈጸሙት ግፍና በደል ሄደዉ ይቅርታ የሚጠይቁት የኢትዮጵያ ህዝብ አካል የሆነዉን የትግራይን ህዝብ ብቻ ነዉ። ደግነቱ የትግራይ ህዝብ በእንደዚህ አይነቱ ቅሌት አያምንም እንጂ ቀድሞዉንም ቢሆን የወያኔ ዘረኞች ለነፃነቱ ለመታገል በረሃ ገባን የሚሉትና ዛሬም ቆመንለታል የሚሉት በአለባሌ አባባላቸዉ “ወርቃማዉ ዘር” እያሉ ለሚጠሩት ለትግራይ ህዝብ ነዉ። ያለፉት ሃያ ሦስት አመታት ስራቸዉና የሰሞኑ የ”ይቅር በሉን” ድርጊታቸዉም የሚያሳየን ይህንኑ ነዉረኛ ተግባራቸዉን ነዉ።
እርግጠኞች ነን የንግድ ባንክ ደንበኛ የሆነ ነጋዴ ገንዘቡን ተሸክሞ አዋሽ ባንክ ገብቶ አስገቡልኝ ብሎ አይጠይቅም፤ ቢጠይቅም አዋሽ ባንክ ወደ ባንክህ ሂድ ይለዋል እንጂ ጥያቄዉን አያስተናግድም። እንደዚህ አይነቱ የባንክ አገልግሎት ደግሞ ዘመናዊ የባንክ አገልግሎት እንግዳ በሆነባት ኢትዮጵያ ዉስጥ ቀርቶ አሜሪካና አዉሮፓ ዉስጥም የለም። ታድያ ለምንድነዉ ሃያ ሦስት አመት ሙሉ የኢትዮጵያን ህዝብ ሲገድሉና ሲያስገድሉ ፤ ሲዘርፉና ሲያዘርፉ የከረሙት ስብሀት ነጋና አባይ ፀሐዬ ትግራይ ዉስጥ በየአዉራጃዉ እየዞሩ ህዝቡን አጥፍተናልና ማረን ብለዉ ይቅርታ የጠየቁት? የእነዚህ ልባቸዉ ያበጠ ዘረኞች የሰሞኑ የ”ይቅር በሉን” ሸር ጉድ ብዙ ነገሮችን እንድናጤን ግድ ይለናል። እኛ ብንወድ ባንወድ፤ ብንቀበል ባንቀበል ወያኔ ሸንጡን ገትሮ የሚሰራዉ እወክለዋለሁ ለሚለዉ ለትግራይ ህዝብ ነዉ። በእርግጥ ወያኔ የትግራይን ህዝብ መብትና ነጻነት እንዲከበር አድርጓል የሚል ቅዠት ዉስጥ የሚገባ ኢትዮጵያዊ ያለ አይመስለንም፤ ሆኖም ወያኔ ስልጣን በያዘባቸዉ ባለፉት ሃያ ሦስት አመታት ዉስጥ የትግራይን ህዝብና ሌላዉን ኢትዮጵያዊ በኤኮኖሚዉና በፖለቲካዉ መስክ በእኩልነት ተመልክቷል የሚል የለየለት የቀን ቅዠት ዉስጥም አንገባም። ይህንን ለማረጋገጥ ደግሞ ብዙ መዝገብ ማገላበጥ ወይም ሃያ ሦስት አመት ወደኋላ መጓዝ ያለብን አይመስለንም ። ወያኔዎች እስክንድር ነጋን፤ ባለቤቱን ሰርካለም ፋሲልን፤ ሲሳይ አጌናንና ሌሎችንም ጋዜጠኞች አስረዉ ሲፈቱ፤ እነ ሲሳይንና አነ እስክንድርን የንግድ ፈቃዳቸዉን ቀምተዉ ዳግመኛ ወደ ህትመት ስራ እንዳይመለሱ ሲያደርጉ ምንም ቢሆን የኛ ነዉ የሚሉትን ግን ያለምንም ችግር ጋዜጣዉን እያተመ እንዲኖር ፈቅደዉለታል፤ ደግሞም ሊገድሉኝ ነዉ ብሎ ከአገር ከኮበለለ ከሁለት አመት በኋላ አገር ቤት ሲመለስ እጃቸዉን ዘርግተዉ ተቀብለዉታል። ጋምቤላ ዉስጥ አኝዋኮችን ከአያት ቅድመ አያቶቻቸዉ መሬት ላይ አፈናቅለዉ መሬቱን ለትግራይ ባለሀብቶች ሰጥተዋል።

የትግራይ ባለኃብቶና የንግድ ድርጅቶቻቸዉ ባሰኛቸዉ ክልል እየሄዱ አትራፊ መስኮችን እየመረጡ እንዲሰሩ ይፈቀድላቸዋል፤ ሌላዉ ኢትዮጵያዊ ግን ለነሱ ካልገበረ ወይም ካልሰገደ በራሱ ክልልም ያሰኘዉን ስራ መስራት አይችልም። ኢትዮጵያ ዉስጥ በየመንደሩ እንደጦር የሚፈሩትና በየመስሪያ ቤቱ ጎንበስ ቀና የሚባልላቸዉ የየመስሪያ ቤተ ሀላፊዎች ሳይሆኑ በየደረጃዉ የተቀመጡ የትግራይ ተወላጆች ናቸዉ። ወታደርና ፖሊስ ዉስጥም የትግራይ ተወላጅ የሆነ መቶ አለቃ ሌላዉን ሻምበልና ሻለቃ እንዳሰኘዉ መዘርጠጥ ይችላል። ከዚህ በተጨማሪ በየትምህርት ቤቱና በየማሰልጠኛ ተቋሞቹ ዉስጥ በትግራይ ተማሪዎችና በኦሮሞ ተማሪዎች እንዲሁም በአማራ ተማሪዎችና በትግራይ ተማሪዎች መካከል ግጭት ሲፈጠር የጸጥታ ኃይሎች ግጭቱን ከማብረድ ይልቅ የትግራይ ተማሪዎች ከለላ ሲሆኑ በተደጋጋሚ ታይቷል። የትግራይ ተወላጆች ከትግራይ ክልል ዉጭ በደል ቢፈጽሙም በፈጸሙት በደል ልክ እስር ቤት አይገቡም፤ ድንገት ቢገቡም ዋስትና አይከለከሉም፤ ቢታሰሩ ደግሞ እስር ቤት ዉስጥ ብዙ አይቆዩም። በሌላ በኩል ደግሞ የትግራይ ተወላጆች ከሌሎች ኢትዮጵያዉያን በተለየ ሰለሚታመኑ በፖለቲካ፤ ወታደራዊና ሲቪል ተቋሞች ዉሰጥ ቁልፍ የሆነ የሀላፊነት ቦታ የሚሰጠዉ ለእነሱ በቻ ነዉ። ለምሳሌ የቦሌ አዉሮፕላን ማረፊያን የደህንነትና ሌሎቹንም ቁልፍ ቦታዎች እንዳለ የሚቆጣጠሩት የትግራይ ተወላጆች ስለሆኑ አንድ ሰዉ አይኑን በጨርቅ ታስሮ ከአሜሪካ ቦሌ አዉሮፕላን ማሪፊያ አርፎ ኢሚግሬሺን ዉስጥ ቆይቶ አታልፍም ተብሎ ቢመለስ መቀሌ ሄጄ አትገባም አሉኝ ይላል እንጂ አዲሰ አበባ ያረፈም አይመስለዉም። እንደዚህ አይነቱ አይን ያወጣ ዘረኝነት ወያኔን በሩቁ የሚያዉቁ ወገኖች ይገርማቸዉ ይሆናል፤ የኢትዮጵያ ህዝብ ግን በገባና በወጣ ቁጥር ስለሚያጋጥመዉ “ቀን የሰጠዉ ቅል ድንጋይ ይሰብራል” እያለ ያማትባል እንጂ በእንደዚህ አይነቱን በየቀኑ በሚያየዉ ትርዕት አይገረምም።

የኢትዮጵያን የዉጭ ምንዛሪ እያራቆቱ አዉሮፓና አሜሪካ ዉስጥ በዉድ ገንዘብ መኖሪያ ቤትና የንግድ ድርጅቶችን ከሚገዙት ኢትዮጵያዉያን ዉስጥ 90% ዎቹ የትግራይ ተወላጆች ናቸዉ። ለህዳሴዉ ግድብ ግንባታ ከሲሚንቶ ጨምሮ የተለያዩ የኮንስትራክሺንና ሌሎችም ለግድቡ ስራ ግብአት የሚሆኑ አቅርቦቶችን የሚያቀርቡት በትግራይ ተወላጆች የተያዙ ኩባኒያዎች ናቸዉ። ከሌላዉ የኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ሲነጻጸር ( ወደ ገጽ 5 ዞሯል )

## ሲቪል ሰርቪስ መስሪያ ቤት የህወሀት ፓርቲ ታማኝ አገልጋይና ስራ ማስፈፀሚያ መሆኑ ታወቀ

የወያኔ/ኢህአዴግ ከፍተኛ ባለስልጣኖች በተካፈሉበትና ሲቨል ሰርቪስ መስሪያ ቤተን በተመለከተ በተካሄደ ዉይይት ሲቪል ሰርቪስ መስሪያ ቤት ለተገልጋዩ ህብረተሰብ፣ ለህዝብ ተቋማትና ለመንግስት ቢሮዎች የአሰራር እንዲሻሻልና ቀልጣፋ እንዲሆን ከማገዝ ይልቅ በፖለቲካ አሰተሳሰብና የፓርቲ ስራዎችን በመስራት የተጠመደ ነው ሲሉ የአገዛዙ ባልስልጣኖች በራሳቸዉ አፍ መናገራቸዉ ተሰማ። ተገልጋዩ ህዝብና የተለያዩ ተቋማት በስርዐት ብልሹነት በማማረር ላይ ባሉበት ወቅት እነዚህን ችግሮች ይቅርፋል ተብሎ በህዝብ ገንዘብ የተገነባዉ ተቋም ህዝብን ሳይሆን የፖለቲካሰ ፓርቲን ማገልገሉ ብዙዎችን አበሳጭቷል። የሚገርመዉ ጅሮ ለባመቤቱ ባዳ እንዲሉ ሆኖ ነዉ እንጂ የኢትዮጵያ ህዝብማ ሲቪል ሰርቪስ መስሪያ ቤት የሚያመርታቸዉ ሰዎች የፓርቲዉ ሰዎችን እንደሆነ ያወቀዉ ገና ከጧቱ ነበር፤ ለዚህም ነዉ ይህንን በህዝብ ላይ የሚቀልዱ ካድሬዎችን እያመረተ የሚያወጣዉን ተቋም “ ዲንጋይ ማምረቻ” ብሎ የሰየመዉ።የሲቪል ሰርቪስ ስራዎች ሳይሰሩ እንደሚቀሩ ተመልክቷል፡፡

ተገልጋዮች በአግልግሎት እጦት እየተማረሩ እና እየተሰቃዩ መሆናቸውን እየገለጹ መሆኑን በተደጋጋሚ ከገለጹ በሁዋላ ነው፣ የስድስት ወራት የስራ አፈጻጸም እና የሴክተር መስሪያ ቤቶች ለምርጫ 2007 ያላቸው ዝግጁነት በሚል ርዕስ ውይይት የተደረገው፡፡ ተወያዮቹ፣ የሲቪል ሰርቪስ አደራጃጀት አብዛኛውን የመንግስት ሰራተኞች የኢህአዴግ ቲፎዞ እንዴት ማድረግ ይቻላል? በሚለው ጉዳይ ላይ በስፋት መክረዋል። በመንግስት ሰራተኛው ዘንድ ከፍተኛ የምክክር መድረክ በመፍጠር እና በአሁኑ ስዓት በከፍተኛ ሁኔታ ጥያቄ እየሆነ የመጣውን የኑሮ ውድነት ጥያቄ ለመመለስ ደሞዝ መጨመር እንደሚያስፈልግ በውይይቱ የተነሳ ሲሆን፣ ይህን ከምርጫ 2007 ጋር በማያያዝ ተግባራዊ ማድረግ ኢህአዴግን አሸናፊ ያደርገዋል ተብሎአል።

ትግራይ፤ አማራ፤ ደቡብ እና ኦሮምያ ሲቪል ሰርቪስ ቢሮዎች በተሰጣቸው መመሪያ መሰረት ደሞዝ ማሻሻያ ሰርተው ያጠናቀቁ ሲሆን፣ ኢህአዴግን የምርጫ ስትራቴጂ ተከትሎ ተግባራዊ ለማድረግ መመሪያ እየጠበቁ እንደሆነ በበሮዎች ተወካዩች በኩል ገልፀዋል። የአንድ ለአምስት ስትራቴጅ በመንግስት ሰራተኛው ዘንድ ተቀባይነት ማጣቱ ለሲቪል ሰርቪሱ ፈተና እንደሆነበት የተገለጸ ሲሆን፤ በቀጣይ ለፖለቲካው እንቅፋት ሊፈጥር እንደሚችል ታስቦ፤ በአንድ ለ አምስት ተሳትፎ ያላደረገ እና በሚሰጡት ዙሪያ ውይይት የማያደርግ ሰው የዲሲፒሊን እና የደሞዝ ቅጣት እንዲወሰድበት የሚል ሃሳብ ተነስቷል። የደሞዝ ክፍያ ጭማሪ ነጋዴው በማያውቀው መልኩ ካልተከናወነ እሳት ላይ ቤንዚን እንዳይፈጥር እና በዋጋ ንረት ሃገሪቱ እንዳትመታ እና የታለመው የምርጫ ስኬታማነት አደጋ ውስጥ እንዳይገባ ጥንቃቄ ያስፈልጋል ተብሎአል። ኢህአዴግ የሚመራው የሚቀጥለው ውይይት “የኢህአዴግ ጽ/ቤት በትምህርት፣ በንግድ እና ትራንስፖርት ዘርፍ የሴክተር መስሪያ ቤቶች ለምርጫ 2007 ያላቸው ዝግጁነት” በሚል እንደሚካሄድ ከኢህአዴግ ምንጮች ያገኘነው መረጃ ያስረዳል።

## የሸቀጦች ዋጋ አሁንም ከፍተኛ ነው ሲሉ ሸማቾች ገለጹ

ከሚቀጣጠል እሳት ወደ እንደሚወጣ ጢስ ወደ ላይ እንጂ ወደታች መዉረድ የማያዉቀዉ የኢትዮጵያ ሰቀጦቸ ዋጋ በተለይ ከአብዛኛዉ ህዝብ የመግዛት አቅም ጋር ሲታይ እጅግ በጣም ከፍተኛ መሆኑን የሰሞሙን የፋሲካ በዐል አስመለክቶ ዘጋቢያችን ያነጋገርናቸው ሸማቾች ገልጹ ፡፡ በአዲስአበባ በሾላ እና በሳሪስ ገበያዎች የአንዳንድ ሸቀጦች ዋጋ መጠነኛ መረጋጋት ቢታይባቸውም ከሕዝቡ የመግዛት አቅም ጋር ሲነጻጸር አሁንም ዋጋቸው ውድ መሆኑን በገበያዎቹ ተዘዋውሮ የተመለከተው ዘጋቢያችን የፈረንጅ ሽንኩርት በኪሎ ከ12-14 ብር፣ የአበሻ ሽንኩርት ከ20-26 ብር፣ ነጭ ሽንኩርት ከ40-45 ብር በመሸጥ ላይ መሆናቸውን ገልጿል።

ቅቤ ለጋ የሚባለው በኪሎ ከ170-190፣ መካከለኛ ከ170-180፣ በሳል ከ155-170 ብር እየተሸጠ ሲሆን አንድ ዕንቁላል የአበሻ ከ2 ብር ከ70 ሳንቲም አስከ 2 ብር ከ75 ሳንቲም፣ የፈረንጅ ዕንቁላል ከ2 ብር ከ75 እስከ 2 ብር ከ80 ሳንቲም ፣ በመሸጥ ላይ ነው፡፡ የአበሻ ዶሮ ከብር 120 እስከ 180 የሚሸጥ ሲሆን የፈረንጅ ዶሮ ከ100 እስከ 120 ብር ይገኛል። ታርዶ የተዘጋጀ የአበሻ ዶሮ በየሱፐርማርኬቱ ከ80 እስከ 100 ብር የሚሸጥ ሲሆን፣ የፈረንጅ ዶሮ በኪሎ ከ70-80 ብር ገደማ ይሸጣል። የበግ ገበያ ሙክት የሚባለው ከ2 ሺ ብር በላይ የሚጠየቅበት ሲሆን መካከለኛ በግ ከ1200 እስከ 1500 ብር፣ ጠቦት ከ750 እስከ 1200 ብር እየተጠየቀበት ይገኛል። የሠንጋ ዋጋ የደለበው ከ10 ሺህ እስከ 15 ሺህ ብር እየተጠየቀበት መሆኑን ገልጿል። በበዓሉ ገበያ የቀይ ሽንኩርት ዋጋ ትንሽ ጭማሪ ከማሳየቱ በስተቀር ሌሎች ሸቀጦች የመረጋጋት ሁኔታ ማሳየታቸውን አንዳንድ ያነጋገርናቸው ሸማቾች የገለጹ ሲሆን፣ በአሁኑ ወቅት በገበያዎቹ ያለው ሸቀጦች ዋጋም የተረጋጋ ቢመስልም ግን ከሕዝቡ የመግዛት አቅም አንጻር ሲታይ አሁንም ውድ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

## ሕወሃት ዜጎችን ያለ ርህራሄ መጨፍጨፉን

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

በተተኮሰ ጥይት የሞቱ ከመሆኑም በላይ አንድ የ85 ዓመት አዛውንት በቤታቸው በር ላይ በተቀመጡበት አፋር በመሆናቸው ብቻ በጥይት ተደብድበው መገደላቸው እንደሆነ አጋልጠዋል። ከዚህም በላይ ደግሞ ሟቾቹ በእስልምና ሃይማኖት ስርአት በእለቱ መቀበር ሲገባቸው የሕወሃት ፌደራሎች አስከሬኖችን ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆናቸው ተቃውሞውንና የሕዝቡን ምሬት እንዳናረውና ከከፍተኛ የሞት ሽረት ትግል በኋላ ሕዝቡ በጉልበቱ አስከሬኖችን እንደወሰደ ጨምረው ጠቁመዋል።

ከማረጋጋት ይልቅ ሕዝብ መጨፍጨፍና መግደል የሚቀናው አግአዚ ጦር እርምጃ ከመውሰዱ በፊት ሕዝቡን ለማሳመን በሚል እሁድ ዕለት የተላከው በአፋር ክልል ምክር ቤት አፈ ጉባኤ መሃመድ አምበጣ የተመራ ቡድን በሕዝብ ቁጣና ተቃውሞ ያለ ምንም ውጤት እንዳመጠጡ በፍጥነት ተመልሷል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በትላንትናው እለት ከማእከል ከወያኔ ጉያ የተላኩ ጄኔራል ሙሴ፣ ኮሎኔል ዓለምና አንድ ለጊዜው ስሙ ያልታወቀ የወያኔ ወታደር አፋር ክልል በመግባት ውጥረቱን ለማብረድ ሙከራ እያደረጉ እንደሆነ የታወቀ ሲሆን፤ የወያኔ ፌደራል ጉዳዮች ቁንጮ በተገኘበት የሱማሌና የአፋር ክልል ገዥዎች ችግሩን በፍጥነት ለመፍታት ውጥረት የተሞላበትና ፍርሃት የነገሰበት ስብሰባ በማካሄድ ላይ እንደሆኑ ውስጥ አዋቂ ምንጫችን ከቦታው ተቁሟል። እንደ ውስጥ አዋቂ ምንጫችን ዘገባም ከዚህ እጅግ አስፈሪ፣ ጭቅጭቅ የተሞላበትና አድካሚ ስብሰባ በኋላም በሶማሌ ክልል ላለፉት ብዙ ዓመታት ሕዝቡን በማሰቃየት፣ ሴቶችን በመድፈር፣ ወጣቶችን በመግረፍና በማሰደድ የሚታወቀውና “ልዩ ጦር” በመባል የሚታወቀው የሕወሃት ታዛዥ ጦር በስውር ወደ አፋር ክልል እንዲገባና በሶማሌ የለመደውን በአፋር ሕዝብ ላይ እንዲፈጽም ስምምነት ላይ መደረሱንና ጦሩም በመግባት ላይ መሆኑ ጨምሮ ገልጿል።

በትላንትናው እለት የሁለቱ ክልሎች ገዥዎች ከፌደራል ጉዳዮች የሕወሃት ቁንጮ ጋር በመሆን የመከሩት፤ መሬታችንን ለሶማሌ ክልል ለማስረከብ ነው የሚል ዜና በአፋር ሕዝብ አካባቢ እየተናፈሰ በመሆኑ ሁሉም የማሕበረሰቡ አባላት ካባቶቻችን የወረስናትን መሬታችንን አናስረክብም፣ እናንተ ያሰባችሁት በእኛ ሬሳ ላይ ይፈጸማል፣ ትግስታችን አስጠቃን እንጅ አልጠቀመንም በማለት በከፍተኛ ወኔና እልህ የሚመጣውን እየጠበቁ መሆኑም ታውቋል።

## በአፋር የተነሳውን ተቃውሞ ተከትሎ 8 ሰዎች

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

የፌደራል ፖሊስ የወሰደውን እርምጃ ተከትሎ በአዋሽ ሰባት ኪሎ አካባቢ ህዝቡ ወደ ወደ አውራ ጎዳናዎች በመውጣት ወደ ጅቡቲ የሚሄዱትን መኪኖች ለ12 ሰአታት ያክል አግዷል። የአፋር ክልል ባለስልጣኖች ወደ አካባቢው በመሄድ ህዝቡን ለማነጋገር ቢኖክሩም፣ ህዝቡ ግን አትወክሉንም የሚል መለስ እንደሰጣቸው ታውቋል። 3 የመከላከያ ሰራዊት መኮንኖች በ10 ቀናት ውስጥ ችግሩ እንደሚፈታ ቃል ገብተው የመኪና እገታው እንደተጠናቀቀ የደረሰን መረጃ ያመለክታል።

አንድ ስሟ እንዳይገለጽ የፈለገች የአፋር ተወላጅ የ85 ዓመት አዛውንትን ጨምሮ 8 ሰዎች በአሰቃቂ ሁኔታ መገደላቸውን ማየቷን ከኢሳት ጋር ባደረገችው ቃለምልልስ ገልጻለች አንዲት እርጉዝ ሴትም እንዲሁ ልጇን ሲገድሉባት በልጇ ላይ ስትወድቅ በእርሷም ላይ በተፈጸመ ድብደባ የእርሷም ህይወት አደጋ ላይ ወድቋል። መንግስት ሶማሊያ ገብቶ የሌሎችን ጸጥታና ሰላም ለማስከበር ሲሞክር፣ እኛን ዜጎቹን ግን ረስቶናል በማለት አክላለች ።የአፋር ሰብአዊ መብቶች ተቆርቋሪ ድርጅት ሊ/መንበር የሆኑት አቶ ገአስ አህመድ የሟቾች ስም ዝርዝር እንደደረሳቸው ገልጸው፣ ህዝቡ መንገድ ለመዝጋት የተገደደው በማቾች በመበሳጨታቸው መሆኑን ተናግረዋል። የሶማሌና የአፋር ክልል ድንበሮች ለማካለል በድሬዳዋ ስብሰባ እየተካሄ መሆኑን የተናገሩት አቶ ገአስ የአፋር ህዝብ የራሱን መብት ለማስከበር እንዲህ አይነት እምቢተኝነት አስፈላጊ በመሆኑ የ አፋር ህዝብ ትግሉን እንዲቀጥል እንዲሁም ሁሉም ፓርቲዎችና አለማቀፍ ሰብአዊ መብት ድርጅቶች ከጎናቸው ሆነው ድርጊቱን እንዲያወግዙ ጠይቀዋል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

**መካከኛ ሞገድ:-** በ 358 MB, በ 837 kHz

**አጭር ሞገድ:-** በ 31 MB በ 9700 KHz

**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**

**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org

## ይቅርታ ትዉልድን ማቀራረቢያ እንጂ

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

የደረጃ ዕድገት፤ የስራ ዕድልና በዉጭ አገሮች የከፍተኛ ትምህርት ዕድል በብዛት የሚያገኙት የትግራይ ወጣቶች ናቸዉ። ኢትዮጵያ ከደርግ ዘመን በኋላ ካፈራቻቸዉ ባለሚሊዮኖችና ባለቢሊዮኖች ዉስጥ ከ85% በላይ የሚሆኑት የትግራይ ተወላጆች ናቸዉ። ፌዴራል መንግስት በፕሮጀክት መልክ ከሚያወጣቸዉ ጨረታዎች ዉስጥ አብዛኛዉን በተለይ ትርፉ ትልቅ ከሆነ ሁሉንም ጨረታ የሚያሸንፉት የትግራይ ተወለጆች ናቸዉ። ህንጻ ለመስራት፤ መሬት ለመግዛት ወይም በተለያዩ መስኮች የንግድ ስራ ለመጀመር ማንነታቸዉ ሳይጠናና የመበደር አቅማቸዉ ሳይታይ ከፍተኛ የብድር አገልግሎት የሚያገኙት የትግራይ ተወላጆች ብቻ ናቸዉ። የመከላከያና የደህንነት ተቋሞችን መነካካቱ ወያኔን ማማት ይሆንብናል ብለን ትተነዉ ነዉ እንጂ መከላከያና ደህንነት ዉስጥም ቢዘረዝሩት ጭንቅላትን የሚያሳምም ብዙ ጉድ አለ። እንግዲህ ይታያችሁ አባይ ፀሐዬና ስብሀት ነጋ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ እንዲህ አይነቱን ቢዘረዝሩት የማያልቅ በደል እየፈጸሙ ነዉ ትግራይ ሄደዉ የትግራይን ህዝብ ይቅርታ የሚጠይቁት።!

“ሆድ ያባዉን ብቅል ያወጣዋል” የሚል አንድ ቆየት ያለ የአገራችን ተረት አለ፤ ለወትሮዉ ይህ ተረት የሚተረተዉ ጭምት ሰዉ እየሰከረ ሆዱ ዉስጥ የደበቀዉን ሚስጢር እያወጣ ሲናገር ነበር። ማን አለብኝ ባዮቹና ዕብሪተኞቹ የወያኔ መሪዎች ግን እጥንት የሚሰብር ንግግር እየተናገሩ “ምን አባክ ትሆናለህ” ይላሉ እንጂ ያሰኛቸዉን ለመናገር ብቅልም ስካርም አያስፈልጋቸዉም። ከሰሞኑ ሰብሀት ነጋና አባይ ፀሐዬ ይቅር በሉን ብለዉ ወደ ትግራይ ያደረጉት ጉዞም ከዚሁ ከተለመደዉ የወያኔ “ምንአባክ ትሆናለህ” ከሚለዉ አባባል ተለይቶ የሚታይ አይደለም። እነሱ ጉዞዉን የይቅርታ ጉዞ ይበሉት እንጂ ከዚህ የዘረኞች ጉዞ በስተኋላ ብዙ እብሪት፤ ንቀትና ክፋት አለበት። እነዚህ ዘረኞች የኢትዮጵያን ህዝብ አንገትህን ደፍተህ ካልተገዛህ መኖሪያህ ወይ ቃሊቲ ወይ ቀጨኔ ነዉ እያሉት ሲሆን የተግራይን ህዝብ ደግሞ እኛ ከሌለን መግቢያህን ፈልግ እያሉት ነዉ። እነሱም ቢሆኑ እንደኛ የእግዜር ፍጡር ስለሆኑ ጭንቅላት ተሸክመዋል፤ ችግሩ የእነሱ ጭንቅላት ባዶ በመሆኑ ነገር አልገባቸዉ እያለ ነዉ እንጂ እንኳን እነሱ የእነሱ አያቶች የረዷቸዉ ጣሊያኖችም ቢሆኑ በእስርና በግድያ የኢትዮጵያን ህዝብ ማንበርከክ አልቻሉም። የትግራይ ህዝብም ቢሆን እነዚህ የእንግዴ ልጆች ከመፈጠራቸዉ በፊት የነበረ ህዝብ ነዉ፤ ከእነሱ በኋላም ህልዉናዉ ህያዉ ሆኖ ይቀጥላል እንጂ አደጋ ዉስጥ የሚገባበት ምንም ምክንያት የለም። የወያኔ ዘረኞች የበደሉት የኢትዮጵያን ህዝብ በሙሉ ነዉ፤የትግራይ ህዝብ ደግሞ የኢት ጵያ ህዝብ አካል ነዉና አብሮ ስለተበደለ ይህንን ህዝብ ይቅርታ መጠየቁ በራሱ ጥያቄ ዉስጥ የሚጋበ ጉዳይ አይደለም። ጥያቄዉና ችግሩ ያለዉ እነ ስብሀት ነጋ 94% የሚሆነዉን የበደሉትንና ግፍ የፈጸሙበትን ህዝብ የራስህ ጉዳይ ብለዉ በተናጠል በሌላ አቅጣጫ ያደረጉት የዕብሪት ጉዞ ነዉ። ወያኔዎች ለይቅርታ የተዘጋጀ ልብ ካላቸዉ በዚያ እንደቤት ዉስጥ ዕቃቸዉ በሚቆጣጠሩት ቴሌቪዥን መስኮት ቀርበዉ የኢትዮጵያን ህዝብ ማረን ብለዉ ይቅርታ መጠየቅ አለባቸዉ፤ የትግራይ ህዝብም በዕርምጃቸዉ ተደስቶ ከልቡ ይቅር የሚላቸዉ ያኔ ነዉ።

## የፌዴራል ዋና ኦዲተር ውጭጉዳይና መከላከያ ውስጥ

. . . ( ከገጽ 1 የዞረ )

በብልጫ የተከፈሉ ሂሳቦች ቀረጥ ተከፍሎባቸው ገቢ ለመሆናቸው ማስረጃ ያልቀረበባቸው ሂሳቦች፣ ከበጀት በላይ ወጪ ማውጣትና የመሳሰሉ የሂሳብ አሠራር ግድፈቶች በበርካታ መ/ቤቶች ታይተዋል። የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ አያያዝና አጠባበቅ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ5 መ/ቤቶች ብር 1 ሚሊዮን 272 ሺ 93 ብር ከ33 ሳንቲም የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ሲገኝ፣ ጉድለት የተገኘባቸው ዩኒቨርስቲዎች ተብለው የተጠቀሱት ደግሞ ጂማ፣ ሰመራ፣ ወሎ፣ ባህርዳርና ጅጅጋ ናቸው።

በጉድለት የታየው የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ተገቢው እርምጃ ተወስዶ እንዲተካ ለየመ/ቤቶቹ በተላከው የስራ አመራር ሪፖርት ማሳሰባቸውን ዋና ኦዲተሩ አመልክተዋል። በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በሂሳብ መግለጫ ሪፖርት የተደረገውና በቆጠራ የተገኘው ጥሬ ገንዘብ መካከል በ3 መ/ቤቶች ማለትም በደብረ ማርቆስና ባህርዳር ዩኒቨርስቲዎች እና አላጌ የግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኮሌጅ ቆጠራው በብር 997 ሺ 412 ከ79 ሳንቲም ልዩነት በማነስ የታየ ሲሆን በአጠቃላይ በ24 መ/ቤተችም የተለያዩ የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመቶች እንደሚታዩ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

በሚኒስትሮች ምክር ቤት የፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እስከ 35 በተደነገገው መሠረት የሰነድ ሂሳብ በወቅቱ መወራረዱ ሲጣራ በ77 መ/ቤቶች ብ 877 ሚሊዮን 45 ሺ 264 ብር ከ30 ሳንቲም በደንቡ መሠረት በወቅቱ ሳይወራረድ ገኝቷል። ከዚህ ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት በግብርና ሚኒስቴር የግብርና ቴክኒክ ሙያና ትምህርት ስልጠና ማስተባበሪያ 173 ሚሊዮን 607 ሺ 265 ብር ከ52 ሳንቲም፤ ውጭ ጉዳይ ሚ/ር 149 ሚሊዮን 427 ሺ 709 ብር ከ65 ሳንቲም፤ የትምህርት ሚኒስቴር 100 ሚሊዮን 298 ሺ 362 ብር ከ09 ሳንቲም፤ የሀገር መከላከያ ሚ/ር 97 ሚሊዮን 146 ሺ 944 ብር ከ59 ሳንቲም፤ ግብርና ሚ/ር 77 ሚሊዮን 744 ሺ 994 ብር ከ72 ሳንቲም፤ ጎንደር ዩኒቨርስቲ 32 ሚሊዮን 153, 328 ብር ከ69 ሳንቲም፤ ደብረብርሃን ዩኒቨርስቲ 26 ሚሊዮን 671 ሺ 151 ሺ 92 እና የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት 22 ሚሊዮን 945 ሺ ,234 ብር ከ57 ሳንቲም ይገኙበታል፡፡

ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳቡ ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት በወቅቱ ካልተወራረደ ወይም ካልተሰበሰበ በቆየ ቁጥር የመሰብሰብና ወደ ሀብትነት የመለወጥ እድሉ ተዳክሞ ለብክነት በር የሚከፍት በመሆኑ መ/ቤቶቹ የፋይናንስ ደንብና መመሪያዎችን ተከትለው ገንዘቡን እንዲሰበስቡ ወይም እንዲያወራርዱ ዋና ኦዲተሩ አሳስበዋል። የዕቃና አገልግሎት ግዢ በመንግሥት ደንብና መመሪያ መሠረት የተፈፀመ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፤ በ43መ/ቤቶች ብር 165 ሚሊዮን 892 ሺ 637 ብር ከ56 ሳንቲም የመንግሥትን የግዢ አዋጅ፤ ደንብና መመሪያ ያልተከተለ ግዢ ተፈፅሞተገኝቷል፡፡ ከግዥ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ውጭ ግዥ የፈፀሙ መ/ቤቶች መካል፤ ባህርዳር ዩኒቨርስቲ 32 ሚሊዮን 061 ሺ 100. ብር፤ ጂማ ዩኒቨርስቲ 19 ሚሊዮን 117 ሺ 878 ብር ከ73 ሳንቲም፤ አርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ 18 ሚሊዮን 344 ሺ 467 ብር ከ.23 ሳንቲም፤ ማዕድን ሚ/ር 16 ሚሊዮን 274, ሺ 515 ብር ከ25 ሳንቲም እና አክሱም ዩኒቨርስቲ 14 ሚሊዮን 168, ሺ 410 ከ69 ሳንቲም ይገኙበታል።

ካልተከተሏቸው የግዥ ደንብና መመሪያዎች ውስጥ የጨረታ ማስታወቂያ በማውጣት ሊፈፀሙ የሚገባቸውን ግዢዎችያለጨረታ ማስታወቂያ በመግዛት፤ በዋጋ ማወዳደሪያ መፈፀም ያለበትን ግዥ ውድድር ሳይደረግ መፈፀም እና የውስን ጨረታ የግዥ ዘዴ ተግባራዊ የሚሆነው ግልጽ ጨረታ ሁለት ጊዜ ወጥቶ እቃው በሚፈለገው ጥራትናመጠን ካልተገኘ ቢያንስ አምስት አቅራቢዎች በውስን ጨረታ መጋበዝ የሚለውን ሳያሟሉ ግልጽ ጨረታ ያላወጡና በውስን ጨረታው የግዥ ዘዴ በቂ አቅራቢዎች ሳይጋብዙ ግዥን ማከናወን የሚሉት ይገኙበታል፡፡ የግዢ መመሪያን ሳይከተሉ ግዢ መፈፀም ለምዝበራና ለጥራት መጓደል ጭምር የሚያጋልጥ በመሆኑ የመንግሥት ግዢደንብና መመሪያን አክብረው በማይሰሩ መ/ቤቶች ላይ የተጠናከረ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል ብሎአል መስሪያ ቤቱ።

ኦዲት በተደረጉት መ/ቤቶች ደንብና መመሪያ ተጠብቆ ክፍያ መፈፀሙ ሲጣራ በ41 መ/ቤቶች 75 ሚሊዮን 992 ሺ 434 ብር ከ84 ሳንቲም ከደንብና መመሪያ ውጭ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ በደንብና መመሪያ ውጪ አለአግባብ ክፍያ ከፈፀሙ መ/ቤቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ፣ ሀገር መከላከያ ሚኒስቴር 24 ሚሊዮን ብር፤ ጎንደር ዩኒቨርስቲ 10 ሚሊዮን 196 ሺ 507 ብር ከ81 ሳንቲም፤ ጅማ ዩኒቨርስቲ 8, ሚሊዮን 605 ሺ 050 ብር ከ51 ሳንቲም፤ መቀሌ ዩኒቨርስቲ 7 ሚሊዮን 190 ሺ 691 ብር ድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ 6 ሚሊዮን 62 ሺ 182 ብር ከ75 ሳንቲም እና ሚዛን -ቴፒ ዩኒቨርስቲ 4 ሚሊዮን 956 ሺ 941 ብር ከ 47 ሳንቲም ነው።

ከምክንያቶቹም መካከል ከሚመለከተው አካል ሳይፈቀድ የትርፍ ሰዓት ክፍያ በመፈፀም፣ ሰራተኞች መስክ ሳይወጡ የውሎአበል በመክፈልና የአልጋና የምግብ ወጪያቸው በመ/ቤቱ ተሸፍኖ እያለ የውሎአበልበመክፈልና እና የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ሳይፈቅድ የኃላፊነት አበልና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችን ለዩኒቨርስቲ የስራአመራሮች ክፍያ መፈፀም፣ መ/ቤቱን ለለቀቁና ሥራ ላይ ለሌሉ ሰራተኞች ክፍያ መፈፀምና በመሳሰሉት ምክንያቶች ወጪ የተደረገ መሆናቸው በኦዲቱ ተረጋግጧል። በመሆኑም ከደንብና መመሪያ ውጪ ያለአግባብ የተከፈለው ሂሳብ ተመላሽ እንዲሆንና ለወደፊቱም ደንብናመመሪያዎች ተከብረው መስራት እንዳለበት ኦዲት ለተደረጉት መ/ቤቶች ማሳሰቡን መስሪያ ቤቱ አስታውቋል።